መጽሐፍ ቅዱስ ለህፃናት

አቅራቢዎች

# ጴጥሮስና የጸሎት ሐይል፡፡



ጸሐፊው፡ Edward Hughes

ምሣሌ አቅራቢው፡ Janie Forest, Alastair Paterson

ያሻሻለው (አሻሽሎ የጻፈው)፡ Ruth Klassen

የተተረጎመው፡ Zemendale Translation Service
email: zemendale@gmail.com
Po Box 32155, Addis Ababa, Ethiopia

አዘጋጁ፡ Bible for Children
www.M1914.org

©2022 Bible for Children, Inc.
ፈቃድ፡- ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ማባዛት ወይም ማተም ይቻላል ነገር ግን ይህ መሆን የሚችለው ለሽያጭ ካላቀረባችሁ ብቻ ነው።



ሐዋሪያው ጴጥሮስ ስለ ኢየሱስ ለመናገር በሁሉ ስፍራ ይዘዋወር ነበረ። አንድ ቀን ፤ ልካ በሚባል ከተማ ለስምንት አመታት ሽባ ሆኖ በአልጋ ይኖር የነበረን ሰው አገኘው። ጴጥሮስም እንዲህ አለው ፤ “ኢየሱስ ክርስቶስ ይፈውስሃል።ተነሳና አልጋህን አስተካክል።”

ሰውየው በፍጥነት ተነሳ።

ይሔንንም ያዩ ሰዎች ወደ ጌታ ተመለሱ።



አጠገብ ባለች ኢዮጴ በምትባል ከተማም
ሰዎች ሁሉ አዝነው ነበረ። ዶርቃ
የምትባል ክርስቲያን ሴት ሞታ ነበረ።
ወዳጆቿም ለቀብር እንዲሆን ብለው
አዘጋጇት ፤ ሁሉም በአንድ ላይ ወደ
ሚያለቅሱበት በላይኛው ክፍል አደረጉት።



ነገር ግን የዶርቃ ወዳጆች
ጴጥሮስ እዚያ አከባቢ እንደሆነ
ሰሙ፡፡ ወደ ኢዮጴም እንዲመጣ
ብለው ጴጥሮስን ጠሩት፡፡
እርሱም ወደ ላይኛው ክፍል
ሲገባ ፣ መበለቶችም ለእነርሱ
የሚሆን ዶርቃ የሰራቻቸውን
ልብሶች አሳዩት፡፡ ሁሉም ሰው
ይጮህ ነበረ፡፡

ነገር ግን ጴጥሮስ ሁሉንም ወደ ውጪ አስወጥቶ ፣ ተንበረከከና ጸለየ፡፡ ወደ ሟቿም ዘወር ብሎ ፣ “ዶርቃ ሆይ ፣ ተነሺ” አላት፡፡ እርሷም አይናን ገለጠች ፣ ጴጥሮስንም ስታየው ፣ ተነሳች፡፡





ከዚያም እጁን ሰጣትና
አነሳት ፤ ቅዱሳኑንና
መበለቶቹን ሲጠሩ ፣
እንደነቃች አገኟት፡፡ ይሔም
በኢዮጴ ሁሉ ተሰማ ፤
ብዙዎችም በጌታ አመኑ፡፡

ጴጥሮስም በኢዮጴ ከባሕር አጠገብ ባለ ቤት ውስጥ ብዙ ቆየ ፡፡
አንድ ቀን ጴጥሮስ በቤቱ ሰገነት ወዳለ ስፍራ ሊጸልይ ወጣ፡፡
የከተማይቱን ቅጥር ቢመለከት ኖሮ ፣ እርሱን ሊፈልጉ

የሚመጡ ሶስት ተጓዦችን
ያያቸው ነበረ፡፡




እነዚህ ሰዎች እግዚአብሔርን ለሚያመልክ ፤ ቆርኖሊዮስ ለሚባል
የሮማ ወታደር ለሆነ ሰው አገልጋዮች ነበሩ። በራዕይ መልዐኩ
ነግሮታልና ፤ ቆርኖሊዮስ ጴጥሮስን እንዲያገኙ አገልጋዮቹን
ላካቸው ፤
"ለጴጥሮስ ላኩልኝ ።
እርሱም ፤ስምኦን ከሚባል
ቁርበት ሰፊ ቤት ከባሕር
አጠገብ አለ ፤ እርሱም ምን
ማድረግ እንዳለባችሁ
ይነግራችኋል።"

ጴጥሮስም በቤቱ የላይኛው ክፍል በጸሎት እንዳለ ፣ እግዚአብሔር ራዕይን ላከለት፡፡ እርሱም ትልቅ ሹማ ከሰማይ ሲወርድ ይመስላል፡፡ በሸማውም ላይ እንስሳትና አዕዋፋት አሉ፡፡ ጳጥሮስም ያ ንጹሕ አለመሆኑን ያውቃል፡፡ ይሔም ማለት ሐይማኖተኛ አይሁዳዊያን እንዲያ አይነቱን ነገር አይመገቡም ነበረ፡፡ በድንገትም ፣ ወደ እርሱ ድምጽ መጣ፡፡ “ተነስ ፣ ጴጥሮስ ፣ ግደለውና ብላው፡፡”



ጴጥሮስም ለጌታ አለው ፣ “በፍጹም ጌታ ሆይ፡፡” “እኔ እንዲህ ያለውን ተራ እና ንጹሕ ያልሆነውን ነገር አልመገብም፡፡” ለሁለተኛ ጊዜም ድምጽ መጣለት፡፡ “እግዚአብሔር ያነጻውን የምታረክስ አንተ ማነህ;” የሔም ሶስት ጊዜ ሆነ፡፡ ከዚያም ሸማው ወደ ሰማይ ተወሰደ፡፡





ጴጥሮስም ራዕዩ ስለምን እንደሆነ አላወቀም ነበረ። ስለራዕዩ ሲያስብ ፣ እግዚአብሔርም ሶስት ሰዎች እየፈለጉት እንደሆነ እና አብሯቸው መሔድ እንዳለበት ነገረው። ሶስቱም ሰዎች ለቆርኖሊዮስ ቅዱስ መልዓክ ተገልጦ ፣ ወደ እርሱ እንዲልካቸው እንደተናገረው ሲነግሩት ፣ ጴጥሮስም እግዚአብሔር እየመራው እንደሆነ አወቀ።

በቀጣዩም ቀን እርሱና ስድስት ጓደኞቹ ወደ ቆርኖሊዮስ ቤት ሔዱ።



ምንአልባት ፣ አይሁዳዊ
ወዳልሆነ ሰው ቤት ሲመሩት ፣
እግዚአብሔር ሁሉም ሕዝብ
ኢየሱስ የአለም አዳኝ መሆኑን
እንዲያው መፈለጉን ጴጥሮስ
ተገነዘበ፡፡ ጴጥሮስ ሲደርስ ፣
ቆርኖሊዮስ ወድቆ ሰገደለት፡፡

ጴጥሮስም ቆርኖሊዮስን አለው ፣ “ተነስ ፤ እኔ ራሴ ሰው ነኝ።” በቤት ውስጥ ላሉ ሰዎች ሁሉ ነገራቸው ፣ “አንድ አይሁዳዊ ለሆነ ሰው ከአሕዛብጋ አብሮ ለመሆንና ለመተባበር ሕግ እንደማይፈቅድ ታውቃላችሁ አይደል!” “ነገር ግን እግዚአብሔር ማንነም ሰው ንጹሕ ያልሆነና ተራ ነው ብለን እንዳንጠራ አሳየኝ።”



ጴጥሮስም ለእነዚህ አይሁዳዊ ላልሆኑት ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነና ፣በመስቀል ላይ እንደሞተ ፣ የአለም አዳኝ ለመሆንም ከሞት እንደተነሳ ነገራቸው፡፡ መንፈስ ቅዱስም በሁሉም ላይ ወረደና እግዚአብሔርንም ያመሰግኑ ጀመር፡፡ የጴጥሮስ ስድስት ጓደኞችም እጅግ ተደነቁ፡፡ ይሔም የጰንጤቆስጤን ቀን ይመስል ነበረ፡፡ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ አይሁዳዊያን ለሆኑትም ሁሉ ነበረ፡፡ ከዚያም ጴጥሮስ አዳዲሶቹን አማኞች አጠመቃቸው፡፡



በኢየሩሳሌምም ፣ አሕዛብን ስለጎበኘ ጴጥሮስን ተቃወሙት፡፡ ጴጥሮስም ፣ እርሱና ቆርኖሊዮስ በጸሎት ስለተቀበሉት ራዕዮች ነገራቸው፡፡ እነዚህን ነገሮች ሲሰሙ፣ የኢየሩሳሌም ክርስቲያኖች ዝም አሉ፡፡ በጸሎት ወስጥ የእግዚአብሔር ፍቅር ለሰው ሁሉ እንደሆነ ያሳያቸውን ፣ እግዚአብሔርን አከበሩት፡፡



ጴጥሮስና የጸሎት ሐይል።

ይህ ታሪክ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል
በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

ሐዋ 9-12

“የቃልህ ፍቺ ያበራል.”
መዝሙረ ዳዊት 119:130

# መጨረሻ

ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ የሚያስተምረን ግሩም ስለሆነው አምላካችን
እግዚአብሔር እኛን በመፍጠሩ እሱን እንድታውቀው ነው።

እግዚአብሔር “ኃጢአት” ብሎ የሚጠራውን ክፉ ነገር እንዳደረግን ያውቀዋል።
የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው ነገር ግን እግዚአብሔር በጣም ስለወደደን
አንዱንና ብቸኛው ልጁን ለቀራኒዮ መስቀል ሞት አሣልፎ በመሥጠት
እንዲሞትና የኃጢአታችንን ዋጋ በእኛ ምትክ በመሞት እንዲከፍል አደረገው።
ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ በኋላ በምድር ላይ ቆይቶ ወደ ሠማይ ወደ አባቱ አረገ!
ያላመንን እኛም በኢየሱስ አዳኝት ብናምን እና ኃጢአታችንን ይቅር እንዲል
ብለምነው ይቅር ይለናል። ደግሞም ያደርገዋል። እሱም በእኛ ውስጥ ይኖራል፤
እኛም በእርሱ ውስጥ ለዘላለም እንኖራለን አሜን።

ይህ እውነት እንደሆነ ካመናችሁ፣ እግዚአብሔርን እንዲህ በሉት
ጌታ ኢየሱስ ሆይ አንተ አምላክ እንደሆንክ አምናለሁ ነገር ግን ለእኔ ኃጢአት
ለመሞት ስትል ሰው ሆንህ አሁን ደግሞ ህያው ነህ። እባክህ ወደ ህይወቴ ግባ
ኃጢአቴን ይቅር በል በዚህም አዲስ ህይወት አሁን ይኖረኛል አንድ ቀን
ከአንተ ጋር ለዘልዓለም ለመኖር ወደ አንተ እመጣለሁ። ለአንተ እንድኖርና
እንደ ልጅ እንድታዘዝልህ እርዳኝ። አሜን።

በየዕለቱ መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ ከእግዚአብሄር ጋር ተነጋገር! የሐ. 3.16